# በእኛ ወንዝ ላይ ያለውን የውሃ ብክለት ቅነሳ በመለዋወጥ የውሃ ክፍያዎን መቆጠብ ይፈልጋሉ?

## ስለዚህ ሀብት ይወቁ።

ከዝናብ ውሃ ከሚመጣ ብክለት እንደ አረንጓዴ ጣሪያ፣ አስተላላፊ ንጣፍ፣ የዝናብ አትክልት ስፍራዎች እና የዝናብ በርሜሎችን የመሳሰሉ አረንጓዴ ፕሮጀክቶችን በንብረታቸው ላይ በመጠቀም ነዋሪዎች፣ ስራዎች እና የንብረት ባለቤቶች ከ DC Water ክፍያቸው ላይ ገንዘብ ሊቆጥቡ ይችላሉ። እኛ—የዲሲ መንግስት— **እስከ 55% ቅናሽ** በእርስዎ የ DOEE የዝናብ ውሃ ክፍያ ላይ እንዲሁም **እስከ 20% ቅናሽ** ምን ያህል የዝናብ ውሃ የአረንጓዴ ፕሮጀክቶችዎ እንደከለከልዎ ላይ በመመስረት ለንጹህ ወንዞች የማያስተላልፉ አካባቢዎች ክፍያ ያቀርባል።

ይህ ፕሮግራም RiverSmart Rewards ሲባል የቀረበውም በኢነርጂ እና አካባቢ ዲፓርትመንት ነው።

## ብቁ መሆንዎን ያረጋግጡ።

እነዚህ መግለጫዎች **በሙሉ** እውነት ከሆኑ፣ እርስዎ ብቁ ነዎት ማለት ነው፡

- እርስዎ ወይም በቤትዎ ውስጥ ያለ አንድ ሰው የአሁን የ DC Water ደንበኛ ነው። የእርስዎ DC Water ክፍያ የዝናብ ውሃ ክፍያዎችን እንዲሁም ንጹህ ወንዞች የማያስተላልፍ አካባቢ ክፍያን ያካትታል።
- በሁሉም DC Water ክፍያዎችዎ ላይ ወቅታዊ ነዎት።
- በዲሲ ውስጥ ባለው ንብረት ላይ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ብቁ የሆኑ የአረንጓዴ ፕሮጀክቶች አይነት ዘርግተዋል ወይም መጠበቅዎን ቀጥለዋል።
    - የዝናብ ውሃን ለመያዝ የሚያስችሉ ተክሎችን እድገት ለመርዳት የሚሆኑ **አረንጓዴ ጣሪያዎች**፣
    - በኋላ ላይ ለምሳሌ የአትክልት ቦታዎን ለማጠጣት የሚሆን የዝናብ ውሃ የሚያጠራቅምና የሚይዝ **የዝናብ በርሜል** ወይም ሲስተርን
    - በአስፋልት፣ ኮንክሪት ወይም የሸክላ ገጽ ምትክ የዝናብ ውሃ ለመያዝ እና በጊዜያዊነት ለማጠራቀም**የአስተላላፊ ንብርብር ሲስተም**፣
    - የዝናብ ውሃን ለማጠራቀም እና የተበከለውን ለማጣራት **የዝናብ አትክልት ስፍራዎች** ወይም ተመሳሳይ ሲስተም፣
    - በአፈር ላይ የዝናብ ውሃ ማቆየትን ለመርዳት**የጥላ ዛፎች**
    - ወደ መንገዱ ንጣፍ ከሚፍሰስ ወደ ሳሩ አቅጣጫ እንዲፈስስ አቅጣጫ በማስቀየር **የተለያየ የውሃ መውረጃ ቱቦ።**

ሁለቱም የቤት ባለቤቶች እንዲሁም ተከራዮች ሊያመለክቱ ይችላሉ።

# ያመልከቱ።

1. ስምዎ ያለበት የቅርብ ጊዜ የ DC Water ክፍያዎች ቅጂ እና የአረንጓዴ ፕሮጀክቶችዎ ፎቶዎችን ያካተቱ ተዛማጅ የሆኑ ሰነዶችን ይሰብስቡ።
2. የዝናብ ውሃን የሚቆጣጠሩበት አካባቢ ስፋት ላይ በመመስረት ከስር ካሉት ሁለት ማመልከቻዎች የትኛው ለእርስዎ እንደሚሰራ ይወቁ እንዲሁም ማመልከቻውን ይሙሉ። የትኛውን መጠቀም እንዳለብዎ እርግጠኛ ካልሆኑ፣ እርዳታ ለማግኘት በ riversmart.rewards@dc.gov ላይ ኢሜይል ያድርጉ።
    - የእርስዎ አረንጓዴ ፕሮጀክቶች ከ 2,000 ስኩዌር ጫማ በታች የሆኑ ውሃ በማያስተላለፉ ገጾች (እንደ ጣሪያዎ እና የመኪና መንገድ ያሉ) ላይ የዝናብ ውሃን የሚቆጣጠር ከሆነ፣ ቀላሉን ማመልከቻ በኦንላይን (ደረጃ #3 ይመልከቱ) ወይም በ ፒዲኤፍ ያጠናቅቁ። ብዙዎቹ የነዋሪ ንብረቶች ይህንን ማመልከቻ ሊጠቀሙ ይችላሉ።
    - የእርስዎ አረንጓዴ ፕሮጀክቶች ከ 2,000 ስኩዌር ጫማ በላይ የሆኑ ውሃ በማያስተላለፉ ገጾች (እንደ ጣሪያዎ እና የመኪና መንገድ ያሉ) ላይ የዝናብ ውሃን የሚቆጣጠር ከሆነ፣ መደበኛውን ማመልከቻ በኦንላይን (ደረጃ #3 ይመልከቱ) ወይም በ ፒዲኤፍ ያጠናቅቁ። ይህ ለመኖሪያ ንብረቶች የተለመደ አይደለም።
3. ማመልከቻዎን በኦንላይን፣ በኢሜይል ወይም በፖስታ ያስገቡ፡
    - በ ኦንላይን ካመለከቱ፣ መለያ መፍጠር ይኖርብዎታል። እባክዎ የኦንላይን ማመልከቻ መመሪያዎችን ይከተሉ።
    - በኢሜይል ለማመልከት፣ የተሞላውን የእርስዎን ማመልከቻ ለ riversmart.rewards@dc.gov ይላኩ። የሰነዶችዎን ፎቶዎች ወይም ስካኖች ወደ ኢሜይሉ እንዲያያይዙ ያስፈልጋል።
    - በፖስታ ለማመልከት፣ ያጠናቀቁትን ማመልከቻ እና የሰነዶችዎን ቅጂዎች አትመው በሚከተለው አድራሻ ይላኩ፡

      Department of Energy and Environment<br>
      Attn: Regulatory Review Division<br>
      1200 First Street NE, 5th Floor<br>
      Washington, D.C. 20002

በማንኛውም ሰዓት ማመልከት ይችላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ።

# ካመለከትኩ በኋላ ምን ይሆናል?

1. ከ 10-20 የስራ ቀናት ውስጥ፣ እኛ—የዲሲ መንግስት—ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገ ልንደውልልዎ ወይም ኢሜይል ልናደርግልዎ እንችላለን።
2. ፕሮጀክትዎ ከ 2,000 ስኩዌር ጫማ በላይ የሆኑ ገጾች ላይ የዝናብ ውሃን ስለሚቆጣጠር መደበኛ የሆነ ማመልከቻ ካስገቡ ወይም የዝናብ ውሃ መቆጣጠሪያ እቅድ ካለዎት፣ ንብረትዎን ለመጎብኘትና የአረንጓዴ ፕሮጀክቶችዎን ለመመርመር መርሃግብር እንይዛለን።
3. በአንድ ወር ውስጥ፣ ተቀባይነት ካገኙ እርስዎን ለማሳወቅ ኢሜይል እንልክልዎታለን። ማመልከቻዎን ለማጽደቅ ከአንድ ወር በላይ ከፈጀብን፣ የፈጀነውን ተጨማሪ ጊዜ ለመሸፈን ቅናሹን ወደኋላ በመመለስ እንተገብረዋለን።
4. ተቀባይነት ካገኙ፣ በ 1-2 የክፍያ ዙሮች ውስጥ ቅናሹን በውሃ ክፍያዎ ላይ ይመለከቱታል።

ተቀባይነት ካላገኙ፣ ኢሜይል እናደርግልዎታለን ወይም እንደውልልዎታለን።

# ሁሉም ብቁ አመልካቾች ቅናሽ ያገኛሉ?

አዎ፣ ከብቁ አረንጓዴ ፕሮጀክቶች ጋር ያሉ ሁሉም አመልካቾች በውሃ ክፍያቸው ላይ ቅናሽ ያገኛሉ።

# ማወቅ ያለብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?

በውሃ ክፍያዎ ላይ ቅናሽ ማግኘትዎን እንዲቀጥሉ፣ ለፕሮግራሙ በየሶስት አመቱ እንደገና ማመልከት አለብዎት። የእርስዎ የአሁን ቅናሽ ጊዜው ከመጠናቀቁ ከሶስት ወራት ቀድመን፣ የማስታወሻ ኢሜይል እንልክልዎታለን። ዳግም ካላመለከቱ፣ ቅናሹን ማግኘት ያቆማሉ። ማስታወሻ ኢሜይሉ ያጠቃለለው ቀላል የዳግም ምዝገባ ማመልከቻ ቅጽ እና መመሪያዎችን ነው።

# ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?

መጀመሪያ፣ ከገጹ ታች ቦታ ላይ የሚገኘውን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ይመልከቱ። አሁንም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ የ RiverSmart Rewards ቡድንን ከሰኞ እስከ አርብ ከ 8 am እስከ 4 pm ባለው ጊዜ ውስጥ በ(202) 671-5004 ላይ ያነጋገሩ። ወይም፣ ለቡድኑ በ riversmart.rewards@dc.gov ኢሜይል ማድረግ እና በርዕሰ መስመሩ ላይ የመንገድ አድራሻዎን (123 A St NE) ማድረግ ይችላሉ።

# በፍጆታዎቼ ላይ አሁንም እርዳታ እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?

በእኛ የፍጆታ ሀብቶች ገጽ ላይ ስለሌላ እርስዎን ሊረዱ ስለሚችሉ መረጃዎች ማግኘት ይችላሉ። በተጨማሪም ቤትዎን የበለጠ ለአካባቢ ተስማሚ ለማድረግ ስላሉት ሃብቶች ማወቅ ይችላሉ።

# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## ለአረንጓዴ ፕሮጀክቶች ለመዘርጋት እና ለመክፈል እርዳታ ማግኘት እችላለሁ?

አዎ! የእኛ RiverSmart Homes ፕሮግራም ዝቅተኛ የሆኑ ዋጋዎች እና ለዝናብ በርሜሎች፣ የዝናብ አትክልት ስፍራዎች፣ አስተላላፊ ንጣፍ እንዲሁም ሌላም ያሉ አረንጓዴ ፕሮጀክቶችን ዝርጋታ። ነጠላ የቤተሰብ ቤት (ወይም አራት ወይም ከዛ በታች ክፍሎች ያሉት ህንጻ) ካለዎት፣ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ማንኛውም አይነት የመኖሪያ ህንጻ፣ የንግድ ህንጻ ወይም የማህበረሰብ ስፍራ ያሏቸው የንብረት ባለቤቶች፣ እኛ —የዲሲ መንግስት— እንዲሁ ለ አረንጓዴ ጣሪያዎች፣ አስተላላፊ ንጣፍ፣ የዝናብ አትክልት ስፍራዎች፣ የዝናብ በርሜሎች፣ እንዲሁም ዛፍ መትከሎች ተመላሾችን እናቀርባለን። የብቁነት መስፈርት፣ የማመልከቻ ሂደት፣ እንዲሁም የተመላሽ መጠን በፕሮጀክቱ አይነት ላይ በመመስረት ይለያያል እንዲሁም ከመገንባትዎ በፊት መተግበር ሊኖርብዎት ይችላል። ከRiverSmart Homes በተለየ ሁኔታ፣ የእኛ ተመላሽ ፕሮግራሞች ለዝርጋታ እርዳታ አያደርግም።

## ይህን ፕሮግራም ከሌሎች ማንኛውም ቅናሾች ወይም ሃብቶች ጋር ማጣመር እችላለሁ?

አዎ! ለዚህ ፕሮግራም ሲያመለክቱ፣ ለእርስዎ በ DC Water ክፍያ ላይ እኛ ወዲያው ለንጹህ ወንዞች የማያስተላልፉ የአካባቢ ክፍያ (CRIAC) የመኖሪያ ቤቶች የእርዳታ ፕሮግራም ለሚባለው ሌላ ቅናሽ እንመዘግብዎታለን።

ለ RiverSmart Homes ከሆነ ወይም ለ አረንጓዴ ጣሪያዎች፣ አስተላላፊ ንጣፍ፣ የዝናብ አትክልት ስፍራዎች፣ የዝናብ በርሜሎች፣ እንዲሁም ዛፍ መትከሎች ተመላሽ ካመለከቱ፣ ለ RiverSmart Rewards ቅናሽ እኛ ወዲያው እንድንመዘግብዎ እንደሚፈልጉ እንጠይቅዎታለን።

## የሚቀበሉትን የቅናሽ መጠን የሚወስነው ምንድን ነው?

የእርስዎን ቅናሽ የምናሰላው በዘረጉት የአረንጓዴ ፕሮጀክት አይነት እንዲሁም መቆጣጠር በሚችለው የዝናብ ውሃ መጠን ላይ ተመስርተን ነው።

## እነዚህ አረንጓዴ ፕሮጀክቶች የዲሲ ከተማን እንዴት አድርገው ሊረዱ ይችላሉ?

እንደ የዝናብ በርሜሎች፣ የዝናብ አትክልት ስፍራዎች እንዲሁም የጥላ ዛፎችን የመሳሰሉ አረንጓዴ ፕሮጀክቶች ንብረትዎን የሚያጥለቀልቀውን እና ወደ ወንዞች የሚፈስሰውን የተበከለ የዝናብ ውሃ መጠን እንዲቀንስ ይረዳሉ። ይህ የ Anacostia ወንዝን፣ Potomac ወንዝን እንዲሁም Rock Creek ከአደገኛ ብክለቶች እንድንጠብቅ ይረዳናል።

## ተቀባይነት ሳላገኝ ብቀር ለፕሮግራሙ እንደገና ማመልከት እችላለሁ?

አዎ። ብቁ የሆኑ የአረንጓዴ ፕሮጀክቶች ከተዘረጉ ወይም አሁን ያለው የእርስዎ አረንጓዴ ፕሮጀክቶች የ DOEE ደረጃዎችን እንዲያሟሉ ከዘመኑ በኋላ፣ ለ RiverSmart Rewards ዳግም ማመልከት ይችላሉ።

## የውሃ ክፍያው በቤቱ ውስጥ በሚኖር በማንኛውም ሰው ስም አይደለም። አሁንም ማመልከት እችላለሁ?

አዎ፣ አሁንም ቢሆን ማመልከት ይችላሉ። የእርስዎ የዲሲ ውሃ ፍጆታ የቤተሰብ አባልን ስም የማይዘረዝር ከሆነ፣ ከቤተሰብዎ ውስጥ የሆነ ሰው የቤትዎ ባለቤት እንደሆነ የሚያሳይ ወይም ከቤተሰብዎ ውስጥ ያለ ሰው ለእርስዎ የዲሲ ውሃ ፍጆታ ክፍያዎች ሃላፊነቱን እንደወሰደ የሚገልጽ የኪራይ ውል ቅጂ ማካተት አለብዎት።

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ኤፕሪል 2021 ነው።*